**እውነተኛ ትግል የሰውን ስም በማጥፋት ላይ አይመሰረትም!**

**ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ 01-25-17**

መቼም ቢሆን የሰው ልጅ ማሰብ ያለበትና ያሰበውንም ሆነ የተመለከተውን ሁኔታ መግለጽ የሚገባው በተረዳውና ባመነበት ልክ እንጂ ሌሎች ሰዎች እንዴት ይረዱልኝ ይሆን እያለ መጨነቅ የለበትም፣ ይህም ሲባል የሌሎችን ባለድርሻዎች አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ምላሽ ግምት ውስጥ ማስገባት የለበትም እያልሁ አይደለም፡፡ አቶ ታዛቢ በቀጥታ ወይም በብሀር ዳሩ ወኪላቸው በአቶ ቀለሙ በለጠ በኩል የእኔን አጠቃላይ ምላሽ መሰረት አድርገው ለመተቸት እንደሞከረው እሱ የሚፈለልገውን ሀሳብ ብቻ ስለሆነ መስማስት የሚፈልገው እኔ በማንኛውም ሁኔታ ፈርቼ እንዳማላውቅና አሁንም ቢሆን ማንንም እንደማልፈራ እሱው ራሱ የመጀመሪያውን ረድፍ የሚይዝ ምስክር ሆኖ ሳለ ለምን ፈራሁ ትላለህ ብሎ ለመጠየቅ ይሞክራል፡፡

አንተም ሆንህ አቶ ታዛቢ ይህንን ጽሁፍ የጻፋችሁትም ቢሆን ታዛችሁ ወይም ለጥቅምና ለስልጣን ማግኛ የሚሆን አጀንዳ አገኘን ብላችሁ አሊያም በጠባብ ብሔረተኝነት ስሜት ታውራችሁ ካልሆነ በስተቀር እናንተ እኔ ላይ ለመደፍደፍ የሞከራችሁትን ድርጊት ፈጽሜው እንደማላውቅም ጠፍቷችሁ አይደለም፣ አቶ ቀለሙ በለጠ ያለህበትን ቦታ ባህር ዳር ብታስመስልም ብአዴንን ወክለህ ወይም ለአማራ ህዝበ ተቆርቁረህ አሊያም የእኔን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ህወሀትና ብአዴን ይቃቃራሉ ብለህ አምነህ ያንን ለማስተካከል አስበህ አይመስለኝም፡፡ ምናልባትም ቦታ ቀያሪ ሌላኛው ታዛቢ ይናገር እንደሆንህም በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡

በዚህ ጽሁፌ ለአንተም ሆነ ለመሰሎችህ አሉባልታና ዝባዝንኬ መጣጥፎች ዝርዝር መልስ ልሰጥ አልፈልግም፣ ያን ላድርግ ብልም ጊዜ የለኝም፣ ሆኖም በአንዳንዶቹ ወጥ የረገጡ ሀሳቦች ላይ ትንሽ ማለት ስላለብኝ እጅግ በተጣበበ ጊዜ ውስጥ ሆኜም ቢሆን ብዕሬን ከወረቀት ለማገናኘት ተገድጃለሁ፡፡ የሚያሳዝነው ነገር አቶ ቀለሙ በለጠና መሰሎቹ ሁሉንም ነገር ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር የማያያዝ አባዜ ያላቸው በመሆኑ "በሀገሪቱ ቁጥር አንድ ዩኒቨርስቲ የልማታዊ አስተሳሰብ መቅረጫ ወይም መገንቢያ ተቋም ውስጥ ገብተህ ትውልድን "በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ትቀርፃለህ" ተብለህ የምትጠበቀው ምሁር ተብየ"

በማለት ያለምንም ማመንታትና ሀፍረት በድፍረት ተነሳስቶና ይሉኝታ እንኳ ሳይፈራ እንደ የዩኒቨርሲቲ መምህርነትህ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህን ማስተማር አለብህ ይህን ካላደርግህ ግን ምሁርነትህ ጥያቄ ውስጥ ይጋባል ከማለት አልፎ አስተሳሰቤንም አበክሮ ሊቃወም ቆርጦ መነሳቱን ያለማመንታት መግለጹ ነው፡፡ ልብ በሉ እኔን ጨምሮ ሁሉም የዩኒቨርሲቲ መምህር የትኛውንም የትምህርት አይነት ስናስተምር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና ልማታዊ ዴሞክራሲን አጽንኦት ሰጥተን ማስተማር አለባችሁ እያለን ነው፣ እኔ

ደግሞ የማስተምረው የህግ፣ የሰብአዊ መብትና የፌዴራሊዝም ጽንሰ ሀሳቦችን ነው፡፡ በአቶ ቀለሙ በለጠና መሰሎቹ እምነት ከሆነ ግን አብዮታዊ ዴሞክራሲና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በየትምህርት ክፍሉ ያለከልካይ እየገቡ በትምህርት መልክ መሰጠት አለባቸው፡፡ ይህ እምነት በራሱ የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ ከሚያራምድ አገር ግንባር ቀደም ዜጋ በምፍጹም የሚጠበቅ አይደለም ብቻ ሳይሆን የትምህርት አሰጣጥ ገለልተኝነት መርህንም ይጻረራል፡፡

አቶ ቀለሙም ሆነ መሰሎቹ እንደዚህ የሚያስቡ ከሆነ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚያስፈልገው በየመስኩ የተማረ ሰው ሳይሆን በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተጠመቀ አብዮታዊ ካድሬ ነው ማለት ነው፡፡ አቶ ቀለሙ አለማፈሩ እንጂ የእኔን ምሁርነት ከአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አንጻር መዝኖ ከመጠራጠሩ በፊት የስራ ባለደርቦቼን ብቻ ሳይሆን እዛው ባህር ዳር የሚገኙትን የቀድሞ ተማሪዎቼን ቢጠይቅ እውነታውን በግልጽ ይነግሩት ነበር፣ ታዲያ ምን ያደርጋል ሰውን እንዲሁ በስሜት ተነሳስቶ እንዳሻው መዘርጠጥና ስም ማጠልሸት እንጂ የተማረው ሀሳቡን በማስረጃ አስደግፎ በመከራከር ማሳመንና ለሌላውም ሰው ትምህርት በሚሆን መልኩ ጨዋነት በተሞላበት አኳኋን ማቅረብንማ ከየት አምጥቶት?

አቶ ቀለሙ ለመሆኑ ልማታዊ ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ለአምባገነኖች የሚያገለግል አይነተኛ መሳሪያ እንደሆነስ በአግባቡ ታውቅ ይሆን? ወይስ ኢህአዴግ አሁን ላይ ደርሶ የአውራ ፓርቲ ቦታን በመያዙ ብቻ ቀጣዮቹን ሰላሳና አርባ አመታት በስልጣን ላይ ለመቆየት ያለውን ፍላጎት እውን ለማድረግ ስለፈለገ የልማታዊ ዴሞክራሲ መርህን መከተል ጀምሬያለሁ ስላለ ያው በጭፍን ደጋፊነት መቀበል የለመድኸውን አሁንም ሳታላምጥ ዝም ብለህ ስለዋጥኸው ነው እንጂ ይዘቱን ተረድተህና ጠቃሚነቱን ተገንዝበህ አይመስለኝም አሁን ላይ በድፍረት ሰውን ለመወንጀያነት አድርገህ ጭምር የምታወራለት፡፡

ምናልባት ረስተኸው ካልሆነ (በትግሉ የነበርህ ከሆነ ማለቴ ነው) በስተቀር ኢህአህዴግ በረሀ በነበረበት ወቅት እኮ የሶሳሊስምን አብዮት አካሂዳለሁ ስለሆነም የማሌ ሀይሎች ተደራጅተው አብዮቱን በግንባር ቀደምነት ሊመሩ ይገባል በሚል እሳቤ ማርክሲስት ሌኒንስት ሊግ ትግራይ (ማሌሊት)፣ የኦሮሞ ማርክሲስት ሌኒንስት ሀይል (ኦማሌሀ) እና የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ሀይል (ኢማሌሀ) የሚባሉ ኮመኒስት ፓርቲዎች ተቋቁመው አንድ ላይ በመሆን ደግሞ የኢትዮጵያ ላብ አደር ድርጅቶች ሀይል (ኢላድሀ) በሚል ስያሜ ልክ እንደ ኢህአዴግ ጥምረት ፈጥረው እስከ 1983 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ መንቀሳቀሳቸው ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ መሬቱን ያቅልላቸውና ቀደም ባለው ጊዜ አቶ መለስ እንዳሉት የቀብር ስነ ስርአታቸው እንኳ በአግባቡ ሳይከወን አባላቱም መርዶው በስርአቱ ሳይነገራቸው እንዲሁ በሽፍንፍን አይ እኛ ከዚህ በኋላ ነጭ ካፒታሊዝምን ነው ተግባራዊ የምናደርገው በማለት ታለፈ፡፡ በዚህን ጊዜ እኔን ጨምሮ በርካታ የፓርቲዎቹ

አባላት እንጥላችን ዱብ ነበር ያለው፣ በእጅጉም ነበር ያዘነው፣ እሞትለታለሁ ብለህ በግንባር ቀደምነት የገባህበት ፓርቲ በስርአቱ እንኳ ሳይነገርህ በከፍተኛ አመራሩ ውሳኔ ብቻ ሞቷል ሲባል ድሮስ ምን አይነት ስሜት ሊጠበቅ ይችላል? አሁን ደግሞ ከነጭ ካፒታሊዝም ጋር ፈጽሞ ሊጣጣም የማይችለውንና በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የሚመራ ልማታዊ ዴሞክራሲን አራምዳለሁ አለ፣ ይኸ ሁሉ ሲሆን አንተና መሰሎችህን ጨምሮ ለምን ብሎ የጠየቀ አባል ወይም ካድሬ አልነበረም፡፡

ምክንያቱም ሁሉም ነገር የሚወሰነው በአቶ መለስ የምርምር ሀሳብ ላይ ተመስርቶ ስለሆነ ቃሉ ቃላችን ነውና ችግር የለውም የሚል ጅምላ ስምምነት ስለነበረ ይመስለኛል፡፡ ለመሆኑ ይኸ ምን ማለት እንደሆነ ይገባሀል አቶ ቀለሙ በለጠ (ቀለሜዋ)? ሌላው የአቶ ታዛቢ ይናገር ግልባጭ መሆንህን የሚያሳየው አቶ ታዛቢ ሀሳብህን ነው እየታገለ ያለው ስትል አለማፈርህ ነው፣ አቶ ታዛቢም ሆነ አንተው ራስህ (የመረጃ ምንጫችሁ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን ድንገት የተለያያችሁ ሰዎች ከሆናችሁ ማለቴ ነው) ሀሳቤን ሳይሆን እየታገላችሁ ያላችሁት መሬት ላይ የሌለና የቅርብ የስራ ሀላፊዎቼም ሆኑ የስራ ባለደርቦቼ ብለውኝ የማያውቁትን የሀሰት ውንጀላ በማቅረብ ስብዕናየን ለማጥቃት ፈረንጆቹ እንደሚሉት ካራክተር አሳሰኔሽን እኮ ነው እያካሄዳችሁ ያላችሁት፡፡

ለዚህም ነው የተሳሳተ መረጃ በመያዝ አንድ ጊዜ ሲሳይ ትግሬ ሆኖ እያለ በትግራዮች ላይ የጥላቻ ስሜት አሳደረ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአማራ ህዝብ ስም እየነገደ ነው ወዘተ ለማለት የምትሞክሩት፣ የዚህ አይነቱ አመለካከት አበው እንደሚሉት ብጥለው ገለበጠኝ የሚሉት አይነት መሆኑ ነው፡፡ የድፍረትህ ድፍረትና የጠማማነትህ ደረጃ ምን ያህል የከፋ መሆኑን ለማሳየት ቃል በቃል ለማለት የፈለግኸውን ሀሳብ እንደሚከተለው ላቅርብ “የአኗኗር ዘይቤህን ከአማራ ህዝብ ነጥለህ አጭበርብረህ በገዛሀት ዘመናዊ መኪና እየተንፈላሰስህ ህዝቤ ሆይ!! ዳቦ ቤትና ታክሲ ተራ መሰለፍ ምን ያደርግልሀል? የጀመርከውን የሚያስጎመጅ የኢኮኖሚ ዕድገት ጣል አድርገህ  ውጣና ጎዳና ላይ ተሰለፍ፤ ጎዳና ላይ  ዕርድ አንቀጥቅጥ ሰልፍ አካሂድ!! እያሉ በፌስ ቡክ መዘባረቅ ብልህነት ነው ጥበብ ነው?”

በሚል መልኩ የዘባረቅኸውስ አይታወቅህም እንጂ አንተው ራስህ ሁነህ ሳለ የአብየን እከክ ወደ እምየ ለከክ ለማድረግ ጥረት አደረግህ፡፡ የአማራን ህዝብ ፍላጎት ለማንጸባረቅና ዘላቂ ጥቅሙን ለማስከበር የሚያደርገውን ጥረት ለመደገፍ የግድ ባህር ዳር መሆን ያለብኝ አይመስለኝም፣ ዘንግተኸው ነው እንጂ በርካታ የብአዴን አመራር እኮ አዲስ አበባ ሆኖ ነው ስራውን የሚሰራው፡፡ አንደኛ ነገር ምንን እንኳ በመሰረተ ልማትe ግንባታና ማህበራዊ አገልግሎቶች በተለይም ትምህርትና ጤና ላይ አበረታች ውጤት ቢመዘገብም የእያንዳንዱን ዜጋ ህይወት በመለወጥ ረገድ የትኛው የሚያስጎጅ ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ተመዝግቦ መው እንዲህ በኩራት ልትለፍፍለት የሞከርኸው?

ይኸ አጋነህ የምታወራለት ዕድገት እኮ በእያንዳንዱ ዜጋ ኪስ ውስጥ ገብቶ ህይወቱን ትርጉም ባለው መልኩ መቀየር ላይ ገና ለውጥ አላመጣም፣ ይልቁንም የኑሮ ውድነቱን በእጅጉ አንሮት አብዘሀኛው የሆነውን ድሀ ህዝብ መፈናፈኛ እንዲያጣ እያደረገው መሆኑን ተረድተኸው ይሆን? ለነገሩ አንተ የህዝብና የመንግስት ሀብት ያለገደብ እየተጠቀምህ ወይም አለቆችህ እየቆነጠሩ በሚሰጡህ እንጀራ ሆድህን እየሞላህ የት ይታወቅህና ነው፡፡

በሌላ በኩል በፌስ ቡክ ገጼ ላይ ለማስተላለፍ የሞከርሁት መልዕክት በጭራሽ ያልገባህ መሆኑን ወይም እንዲገባህ የማትፈልግ መሆንህን የሚያመለክተው ነገር በአንድ በኩል አንድ ኪሎ ሜትር የማይሞላ ቦታ ለመሄድ ወይም ከአስር ደቂቃ የማይበልጥ የእግር ጉዞን የሚጠይቅ አካባቢ ለመድረስ ጭምር በታክሲ ለመጓዝ ጧትና ማታ ተሰልፎ ረዥም ጊዜ ማባከን ጠቃሚ እንዳልሆነና በመደበኛ ስራችንም ሆነ በአካላዊ ጥንካሬያችን ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር ለማስገንዘብ በሌላ በኩል ደግሞ ትንሽም ቢሆን የእግር ጉዞ በማድረግ ጤንነታችንን ለመጠበቅ ጥረት ብናደርግ መልካም ነው ለማለት በማነጻጸሪያነት የቀረበ የሰልፍ ምሳሌ እንጂ አንተ ፍርሀትና ጭንቀት ከወለደውና ኮሽ ሲል ድንግጥ ከሚለው እሳቤህ ተነስተህ አርድ አንቀጥቅጥ የሆነ የተቃውሞ ሰልፍ አድርግ ለማለት ፈልገህ ነው ስትል አጣመህ ተረጎምኸው፡፡

ይኸኔ ይመስለኛል አባቶቻችን ከቂጡ ቁስል ያለበት ውሻ እንደ ልቡ አይጮህም (አይዘልም) በማለት ሀሳባቸውን የሚገልጹት፣ የእኔ ሀሳብ አንተ እንዳልኸው አለመሆኑንማ ሁከትና ብጥብጥ ተፈጥሮ በነበረበት በዛ በመጀመሪያው ቀውጢ ወቅት የሰላም ዋጋው ምን ያህል ነው በሚል ርዕስ የሰላማዊና ህጋዊ የትግል አግባብን ለማስገነዘብ በፌስ ቡክ ገጼ ላይ ያወጣሁትን ጽሁፍ ታነበውና በትክክል ትረዳው ነበር፣ በዚህም አንዳንድ ጽንፈኛ ጸሀፊዎች በዚህ ወቅት እንዴት እንደዚህ ያለ ነገር በመጻፍ በተቀጣጠለው ህዝባዊ ትግላችን ላይ ቀዝቃዛ ውሀ ትቸልስበታለህ? ድሮስ ከወያኔ ምን ይጠበቃል? ወዘተ. የሚል የትችት መአት ወርዶብኝ እንደነበረም ታስታውስ ነበር፡፡

ለነገሩ ያኔ አንተና መሰሎችህ መሸሻችሁን እያመቻቻችሁ ስለነበረ የማንበቢያ ጊዜ አይኖራችሁም፣ ቢኖራችሁም የፍርሀት ቆፈን አላላውስ ብሏችሁ ስለነበር እንደዚህ ዘና ብላችሁ ለመጻፍ አትደፍሩም ነበር፡፡ የእኔን ሀሳብ በአግባቡ የተረዳኸው አለሙሆኑን ወይም አጣመህ ለመተርጎም ቆርጠህ የተነሳህ መሆንህን የሚያሳብቀው ሌላኛው ሀሳብህ ደግሞ "ሲሳይ በዚሁ መጣጥፉ በሰነዘረው አስተያየት ሲብል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ የሴኔት አባል ሆኜ ሰርቻለሁ" አለ በማለት አይን ያወጣ ቅጥፈትህን በግልጽ ማስፈርህ ነው፡፡ እንዳው አንባቢ እንኳ ምን ይለኛል አይባልም እንዴ? እኔ የትኛውም ጽሁፌ ላይ እንደዛ አላልሁም፣ ያልሁት ነገር ቢኖር ግለልጽ ነው እሱም ለሁለተኛ ጊዜ ተመርጩ ሁለት አመት ተማሪዎችን በመወከል ሰርቻለሁ ነው፡፡

ኮሌጅ ውስጥ የቆየሁት ግን በአጠቃላይ አራት አመት መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፣ በዛ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ የተመረጥሁት አንተም ሆንህ አንተን መሰል ውርጋጥ ስም አጥፊዎች እንደምትሉት ደንብ ጥሼና መርህን አፍርሼ ሳይሆን ቀደም ሲል የህግና የኢንጂነሪንግ ተማሪዎችን የኮሌጅ ቆይታ ጊዜ ግምት ውስጥ ሳያስገባ ማለትም ሌሎቹ የትምህርት ክፍሎች በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ትምህርታቸውን ያጠናቅቁ ስለነበር አዲስ ገቢና የመጨረሻ አመት ተማሪ በፕሬዚደንትነት ብቻ ሳይሆን በምክር ቤት አባላነትም ጭምር እንዳይመረጥ የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ ሆኖ እንደነበረ ይታወቃል፡፡

ከዛም ባሻገር በአደረጃጀትም ሆነ በሌሎች ሁኔታዎች መሻሻል የሚገባቸው ሁኔታዎች እንደነበሩ ስራ ላይ የነበረው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማመኑ የምክር ቤት አባላት የቆይታ ጊዜን ጨምሮ የማሻሻያ ስራዎችን ሰራና ለምክር ቤት አቅርቦ አጸደ፡፡ በተለይም የኢንጂነሪንግ ወይም የህግ ተማሪ የሆነ ሰው በምክር ቤት አባልነት ከተመረጠ የሶስተኛ አመት ትምህርቱን እየተከታተለ አዎንታዊ አስተዋጽኦው ግምት ውስጥ ገብቶ በድጋሜ ቢመረጥና ለሁለተኛ ጊዜ ማልገል ቢችል መልካም ነው የሚል ስምምነት ላይ ተደረሰና በዚህ መልኩ ለምን አይሻሻልም የሚል ሀሳብ ቀርቦ በተማሪዎች ካውንስል ሙሉ ድጋፍ አግኝቶ ደንቡ ተሻሽሎ ስራ ላይ ውሎ ስለነበረና ምርጫ ሲካሄድም እኔን ጨምሮ የተወሰኑ የህግና የኢንጂነሪንግ ተማሪዎች እኛ ምረጡን ብለን በመቀስቀሳችን ሳይሆን ስራችንን ተመልክተው በድጋሜ እንድንመረጥ ስለተደረገ እንጂ እኔም ሆንሁ ሌሎቹ የምክር ቤት አባላት በድጋሜ ለመመረጥ አስበንም ሆነ ፈልገን ያሻሻልነው ደንብ አልነበረም፡፡

ይህን ለማድረግም የሚያስችል የተለየ ጥቅም የማይገኝበት መሆኑም ይታወቃል፣ እንዳውም የትምህርትና የጥናት ጊዜያችንን በመሻማት በውጤታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥርብን እንደነበር ሁሉም ተማሪ የሚገነዘበው ሀቅ ነው፡፡ አንተና መሰሎችህ እንደዛ ነው ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ ደግሞ በወቅቱ ተማሪ የነበሩትና አሁን ላይ ሚኒስትር የሆኑ ሰዎችን ጨምሮ በሽዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችና ሁሉንም ተማሪዎች ወክለው ፕሬዚዳንቱንና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን የሚመርጡትን ተማሪዎች አይረቤነትና በእኔ ስሜትና ፍላጎት ብቻ የሚነዱ እንደነበሩ አድርገህ እየገመትሀቸው ነው፡፡

አየህ አቶ ቀለሙ አንድ ጊዜ ስህተት ውስጥ የወደቀና መዋሸት የጀመረ ሰው መጨረሻው እንዲህ እንዳንተ ነው የሚሆነውና የአንዱን ሰው ስም አጠፋለሁ ብለህ መነካካት የማይገባውን ሁሉ እንድትነካካ የሚያደርገው፡፡ ከዚህ ውጭ በእርግጥ አንተ ባልኸው መልኩ ሳይሆን ብአዴን እንደ ድርጅትም ሆነ አብዛኛው የብአዴን አመራርና አባል የእኔን ማንነት ጠንቅቆ ያውቃል፣ ምን አይነት አስተዋጽኦ እንደነበረኝም በአግባቡ ይረዳል፣ በዚህም ምክንያት ይመስለኛል የሚገባኝን ቦታ ሰጥቶና አክብሮ እንድማርና እንድሰራም ያደረገኝ፣ ሆኖም በፖለቲካ አመራርነትና በቢሮክራሲው ውስጥ ሆኜ ትምህርት የመቀጠል እድሌ ውስን እንደሚሆን ስለማውቅና የማስተማር ሞያንም ስለምወድ እድሉን ሳገኝ በስርአቱ አስፈቀጄ ከምስጋና ጋር እንደቅደም

ተከተሉ የመልቀቂያና የመሸኛ ደብዳቤ ተሰጥቶኝ ያንን ይዤ መምጣቴንም አንተም ጭምር በሚገባ ታውቃለህ፡፡ አየህ ምን ያህል በጥላቻ ስሜት ውስጥ ሆነህ እየጻፍህ መሆንህን አንዱ ማረጋገጫ እኔ የአውሮፕላን ቲኬት ቆርጬም ሆነ በአውሮፕላን ቴኬት አጭበርብሬ አላውቅም፣ ምናልባት የዚህችን አይነት አሰራር አንተና መሰሎችህ አድርጋችኋት ይሆናል እንጂ የእኔ ሞራልማ በዚህ አይታማም፡፡ በዛ ላይ አለማወቅህ ነው እንጂ የእኛን የአውሮፕላን ቲኬት የሚቀርጡልን ሾፌሮች ወይም የሂሳብ ክፍል ሰራተኞች ነው የነበሬት፣ እንደዚህ ያለ ተጨባጭ ማስረጃ ቢኖራችሁማ ኖሮ ይህን ጊዜ የእኔ ማረፊያ የት እንደነበር አንተም ጭምር ጠንቀቅህ የምታውቅ ይመስለኛል፡፡

እርግጥ ነው በአንድ ወቅት እኔ የማስተርስ ዲግሪየን ለመከታተል ወደ አዲስ አበባ መጥቼ እያለሁ በጊዜው ፍትህ ቢሮ ውስጥ የነበሩት የአንተ አይነት ስም አጥፊዎች እንደዛ በለው ከማስወራት አልፈው በሀላፊው በኩል ከደሞዝህ ላይ ልንቆርጥ ነው የሚል ደብዳቤ እስከማጻፍ ደረርሰው እንደነበር ይታወቃል፣ ሆኖም ኋላ ላይ ሁኔታው ሲጣራ የእኔ ማጭበርበር ሳይሆን እውነት ሆኖ የተገኘው የሂሳብ ክፍሎች ደረሰኙን በስርአቱ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ቲኬት ኦፊሰሮች ተቀብለው ከፋይል ጋር ባለማያያዛቸው ምክንያት የተፈጠረ ስህተት መሆኑ የተረጋገጠበት ሁኔታ እንደነበረ አስታውሳለሁ፡፡

ከዛ ውጭ የክልሉ አመራሮችማ አንድ አይሉት ሁለት ጊዜ እባክህ አብረን እንስራ በማለት ሊያግባቡኝ ሞክረው ነበር፣ ስለእኔ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖርህ ከፈለግህ ደግሞ በቅርብ የምታገኘው የክልሉ አመራር ካለ እንዲህ አይነት ቅጥፈት የተሞላበት ጽሁፍ ከማዘጋጀትህ በፊት ብትጠይቅ ይሻልህ ነበር፣ በተቃራኒው አንዳንዶቹ በወቅቱ ሲሳይ የእናንተን ስልጣንና መኪና አልፈልግም ብሎ ወደ ዩኒቨረሲቲ ሄደ ብለው ስሜን ያለ አግባብ ሊያጠፉ እንደሞከሩ አስታውሳለሁ፡፡ ይህም ሆኖ የእኔ ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ይኸ የመጀመሪያየ እንዳልሆነ አንተም በሚገባ ታውቃለህ፣ ቀደም ሲል ወደ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገብቼ በመምህርነት እሰራ እንደ ነበረና የክልሉ አመራር እባክህ ወደ ፍትህ ቢሮ ናና አብረን እንስራ ብሎ ሾሞ እንደመለሰኝ ይታወቃል፡፡

ይህም የሆነው እንደ አነተና መሰሎችህ የሰውን ስም በማጠልሸትና ነገር እዛና እዚህ በማመላለስ ከእነሱ ስር አወድውጄ ሳይሆን በአለኝ የአካዳሚክ ብቃት፣ የአመራር ክህሎትና ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ነው፡፡ በህይወቴ ስልጣን ስጡኝ ብየ ተጎናብሼ እንደማላውቅ ይህን ባለማድረጌም በአንዳንድ አመራሮች አካባቢ ይኸ ትቢተኛ አስብሎ ጥርስ እንዲነከሰብኝ ማደረጉ ግልጽ ነው፡፡

ማንም አያስታውሰውም ይሆናል እንጂ በአንድ ወቅት እኮ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር አመራሩን ጨምሮ በየደረጃው ያለው ካድሬ በተለያየ የሞያ መስክ ከመሰልጠን ባሻገር በተግባርም እየተቀያረ እንዲሰራ ይደረጋል የሚል አቅጣጫ ተቀምጦ ነበር፡፡ ነገር ግን በራስ መተማመን የሚሳናቸው ሰዎችና ስልጣንን ሙጭጭ አድርገው በመያዝ በመንግስት መኪናና ቤት ህይወታቸው እስከታልፍ ድረስ መቆየትን የሚመርጡ ወገኖች

መመሪያው እንዳይሰራ አደረጉት፡፡ እኔ ግን በግሌ ገፋሁበትና አንድ አይሉት ሁለት ጊዜ ወደ ዩኒቨርሲቲ በመግባት ብቃቴንም ሆነ ማንነቴን በተግባር ለማሳየት ጥረት አደረግሁ፡፡ ከዛም አልፌ በሞያየ ሌት ተቀን ሰርቼ አንተ እንዳልከው ያን ያህል ዘመናዊ ባትባልም ለስራ የምትሆን ደከም ያለች መኪና ገዝቼ በሷው እዚያና እዚህ ተሯሩጩ ስሰራ በማየትህ አንተና መሰሎችህ አይናችሁ ደም እየለበሰ በክፉ ተመለከታችሁኝ፡፡ ከዛም አልፈህ ለስም ማጥፊያነት ተጠቀምህባት፡፡

የሚገርመው ነገር አዲስ አበባ እንደመጣሁ በነበሩት የመጀመሪያዎቹ አመታት የህዝብ ትራንስፖርት ለመጠቀም ታክሲ ሰልፍ ላላ ቆሜ የተመለከቱ አንዳንድ የክልሉ አመራሮች አቶ ሲሳይ አዲስ መኪና ገዝተን ብንሰጠው የእናንተን ስልጣንና መኪና አልፈልግም ብሎ ይኸው አሁን ታክሲ ሊሳፈር ከህዝብ ጋር ይጋፋል ሲሉ ያፌዙብኝ እንደነበር ሾፌሮቻቸው ሳይቀር በቁጭት ስሜት ውስጥ ሆነው ይነግሩኝ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ በዚች አሮጌ መኪና ተቀናባትና ተንፈላሰስህ ለመባል በቃሁ፡፡ ከዛ ውጭ የእኔን ማንነትና የስነ ምግባር ደረጃ ከፍተኛ አመራሩ ብቻ ሳይሆን አማራ ክልል ውስጥ የሚገኘው መላው የብአዴን አባል ጭምር እንዲሁም የሰራሁባቸው መስሪያ ቤቶች ሰራተኞችም ጠንቅቀው ያውቁታልና በዚህ ረገድ ብዙ አትድከም፡፡

ሌላው ተደጋግሞ የተነሳው ከሶስተኛ፣ ከአራተኛ እና ከሰባተኛ ክፍል ተነስተህ ለዚህ በቅተህ የሚለው ነገር ነው፣ እናንተ ሰዎች ምን ያህል ደደቦችና የደናቁርት ስብስብ እንደሆናችሁ የሚያመለክተው እዚህ ላይ ነው፣ ህወሀት እኮ አምስት የቃታ መሳሪያ ይዞ ለዚህ በመድረሱ ነው የገድሉን ደረጃ ሰማየ ሰማያት ለማድረስ የምትሞክሩት፡፡ አሁን ላይ ከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ላይ የሚገኙት (ሚኒስትሮችና ጀኔራሎችን ጭምሮ ማለቴ ነው) ብዙዎቹ የህወሀትና የኢህዴን/ብአዴን መሪዎች ከሶስተኛና አራተኛ ክፍል ተነስተው አይደለም እንዴ ከድል በኋላ ተምረው ለዚህ የበቁት?

በመሆኑም በእኔ እምነት እነዚህ ሰዎች በእጅጉ ሊደነቁ ይገባቸዋል እንጂ ይህን በማድረጋቸው ሊወቀሱበት አይገባም እኔም ብሆን እንዲሁ፡፡ ለማንኛውም እኔ ከሰባተኛም ተነሳሁ ከሶስተኛ ክፍል አሁን ላለሁበት ደረጃ ለመድረሴ የድርጅቴ ብአዴን/ኢህአዴግ አስተዋጽኦ ቀላል እንዳልሆነ ብገነዘብም የራሴ ጥረት ግን ወሳኙን ቦታ እንደሚይዝ ሳላፍር የምናገረው ሀቅ ነው፡፡ ከድል በኋላ በተለይም በ1984 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ማንም ደፍሮ ስለ ትምህርት ጥቅም ማንሳት ባልቻለበት ወቅት እኮ ነው መሪዎቻችንን እናንተም ተማሩ እኛንም እንድንማር ሁኔታዎችን አመቻቹልን በማለት በአደባባይ መወትወት የጀመርሁት፣ በወቅቱ የነበሩት መሪዎች ምስጋና ይገባቸውና ሀሳባችንን ተቀብለው ሁላችንም እንድንማር ዕድሉን አመቻቹልን፡፡ ይህን እድል በአግባቡ ተጠቅሜ እኔና መሰሎቼ ለዚህ በቃን፣ ታዲያ ይኸ ያስመሰግናል እንጂ በሰይጣናዊ ቅናት መንፈስ ውስጥ ተሁኖ እንዲህ ለመዘለፊያነት ያገለግል ነበርን?

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የእኔ ሀሳቦች ኢህአዴግ ስህተቱን በጊዜ ያርም፣ አባል ድርጅቶቹም ቢሆኑ በተለይም ህወሀትና ብአዴን እንደ ነባርነታቸው የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉና የራያን ህዝብ ጨምሮ ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰብ የህዝቦችን መብት ያክብሩ፣ ችግራቸውንም እህ ብለው ያዳምጡ እና ማንነታቸውን ጠብቀው ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ይፍቀዱ ነው፡፡ እናም አገር እንዲታመስ ያደረገው የእኔ ይህን ማለት ሳይሆን በአሁኑ ወት የኢህአዴግ አመራር ራሱ በግልጽ እንደገመገመውና አሁንም በጥልቅ ተሀድሶ መድረኩ የእየገመገመው እንደሚገኘው ህዝቦች በቅንነት የሚነግሩትን አልሰማ ብሎ እንጂ እኔማ በየትኛው አቅሜ ነው አገር እንዲረበሽ የማደርገው?

ስንተዋወቅ አንተናነቅ እንደሚባለው እኔ ላይ የዚህ አይነት የተቀነባበረ የስም ማጥፋት ዘመቻ የተጀመረው የራያ ህዝብ የማንነት ጥያቄና የማዕከላዊ መንግስታት ምላሽ ከአጼ ዮሓንስ እስከ ኢህአዴግ በሚል ርዕስ ከአለሙ ካሳ ጋር ህወሀት/ኢህአዴግን ጭምር ጠንከር አድርጎ የሚተችና የመፍትሄ አቅጣጫም የሚጠቁም መጽሀፍ አዘጋጅተን በማሳተም ለተደራሲያን ማቅረባችንን ተከትሎ የራያ ህዝብ ለምን ይኸ ሁሉ ግፍና በደል በእኔ ላይ ብቻ ይደርሳል በማለት በድፍረት መጠየቅ በመጀመሩ ይመስለኛል፡፡ ከዛ በኋላ ፌስ ቡክ ላይም ሆነ የተለያዩ ድረ-ገጾችና የግል መጽሄቶች ላይ የምጽፋቸው የዋናው ሀሳቤ ተቀጥላዎች ስለሆኑ ብዙም አስጨንቀዋችሁ አይመስለኝም፡፡

ሌላው በጣም አስገራሚ ነገር የድሮው ሲሳይ የአሁኑ እውነቱ ያቀረብከውን የተቃውሞ ሀሳብ ታስታውሳለህ?? የድርጅት አባል አይደለም፤ ደብዳቤ መተርጎም ሳይችል ቀርቶ (የዩኒቨርሲቲ) ተማሪዎችን ለሁከት ዳርጓል ወዘተ .. ተጨባጭ ያልሆነ የተቃውሞ ሀሳብ አቅርበህ ነበር፡፡ በማለት አሁንም እኔን ከአቶ እውነቱ ዘለቀ ጋር ደርቦ ለመምታት የተጠቀምህበት መረጃ አንተ ልትጠምበት ለፈለግኸ ስም ማጥፋት በትክክል የሚጠቅምህ መሆን አለመሆኑን እንኳ ማገናዘብ አለመቻልህ ሲሆን ይበልጥ ግልብ መሆንህንም ያሳያል፡፡  አንደኛ ነገር አሁንም ደግሜ ላረጋግጥላችሁ የምፈለገው ነገር እኔ ሲሳይ መንግስቴ እንጂ እውነቱ ዘለቀ አይደለሁም፣ ይኸን የምለው ደግሞ ፈርቼ እንዳይመስልህ፡፡

ልብ ብለህ ከተመለከትኸው እኮ አቶ እውነቱ ከሚለው በላይ እኔ እየጻፍሁ አይደለም እንዴ ምኑ ነው የሚያስፈራኝስ? ሁለተኛ ነገር አዎ አንተ ያልኸው ግለሰብ የሆነ ቢሮ ሀላፊ ስለነበረ ብቻ በማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት እንዲመረጥ ሲጠቆም መርህ ላይ ተመስርቼና ተጨባጭ ማስረጃዎችን በማቅረብ ጭምር ተቃውሜ ነበር፣ ምክንያቱም እኔ እስከማውቀው ድረስ በግለሰቡ ላይ የተለየ አመለካከት ኖሮኝ ሳይሆን የድርጅቱ ህገ-ደንብ አባል ያውም ሙሉ አባል ያልሆነ ሰው የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት የለውም ይል ነበርና ነው፡፡ ከዛም አልፎ አንተም እንደጠቀስኸው ከትምህርት ሚኒስቴር የተጻፈን ደብዳቤ በአግባቡ ተርጉሞ ስራ ላይ

ባለማዋሉ ምክንያት ብጥብጥ ተከሰተ፣ በዚህም ምክንያት የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አይንህን ላፈር ብለው ከመድረክ እንዳባረሩት ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ግለሰቡ የከፍተኛ አመራሩ ጠንካራ ድጋፍ ስለነበረው በህገ-ደንቡ ውስጥ የተቀመጠው ጠቅላላ መርህ ወደ ጎን ተብሎ በሚገርም አኳኋን ታዲያ እስካሁን ድረስ አባል ያላደረገው አካል ነው እንጂ ተጠያቂ መሆን ያለበት በሚል አስተያየት ተደግፎ አባል ባይሆንም ይኸ ሰው ስራ ላይ ሊጠቅመን ይችላልና ቢመረጥ ችግር የለውም ብለው ደገፉት፡፡

የሚያሳዝነው በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ሆነና ነገሩ በዛው ጉባኤ ላይ ካስታወስህ አንዲት ጓዲት በተመሳሳይ ተጠቁማ አይ እሷኮ ገና እጩ አባል ነች ተብላ ከአመራሩ አካባቢ ተቃውሞ ስለቀረበባት ሳትመረጥ ቀርታለች፡፡ ይህች አባል ደግሞ ቀደም ሲል አባል ሆና ለረዥም ጊዜ የቆየች ነገር ግን በሆነ አጋጣሚ አቋርጣ እንደገና ወደ አባልነት የተመለሰች ጓዲት መሆኗ እየታወቀ ስላልፈለጓት ብቻ ተቃውሞ አቀረቡባት፡፡ ይህንን አይን ያወጣ አድሎ ምን ትለዋለህ ቀለሜዋ! በመጨረሻም አንተና መሰሎችህ ድርጅቱንም ሆነ ህዝብን በዚህ መልኩ እያሳሳታችሁ ወደ ባሰ ገደል ውስጥ ከምትከቱት ምናለበት እውነተኛውን ነገር ይዛችሁ ስራችሁን ብትሰሩ?

የሰውን ስም ያለ አግባብ ለማጠልሸት የምታጠፉትን ውድ ጊዜም ቢሆን በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ሀገርንና ህዝብን ለመጥቀም ጥረት ብታደርጉ ምናለበት? የማይገጥም ተረትና ምሳሌ ከዚህም ከዛም ለቃቅማችሁ በማምጣት ሰውን ባታሳስቱና እናንተም ከህሊናችሁ ታርቃችሁ ለሌላውም መልካም ምሳሌ ለመሆን ብትንቀሳቀሱ የመጥፎ ሰዎች ምሳሌ ከመሆን ትድናላችሁና እባካችሁ ራሳችሁን ለመሆን ሞክሩ ከዛም በላይ ሀቅን ሳትይዙ እውነተኛ ታጋዮችን በሀሰት እንየወነጀላችሁ ለመደፍጠጥ አትደክሙ፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ስማችሁን እየቀያየራችሁና አንድ ጊዜ ከአዲስ አበባ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከባህር ዳር እያላችሁ በአማራ ክልል ህዝቦችና በብአዴን አባላትና አመራር ስም ባትነግዱ ብሎም እንደዛ ባትቀልዱ እንዲሁም እኔ እከተለው በነበረው በመርህ የመመራት አካሄድ አላግባብ መጠቀም ይፈልጉ የነበሩ ግለሰቦችን ፍላጎት ስለገታ ብቻ እነዚሁ ግለሰቦተች በእኔ ላይ ቅሬታ ይዘው የሚሰጧችሁን የተሳሳተ መረጃ እንደ እውነት ቆጥራችሁ እንናንተም ተሳስታችሁ ሌላውንም ባታሳስቱ መልካም ነው፡፡

ሲሳይ መንግስቴ እንደሆንሁ ማንም ሰው እንደሚያውቀው የሚሰማኝን በግልጽ የምናገርና የምጽፍ ለማንም ማስፈራሪያም ሆነ ስም አጥፊ ያልተገባ ፍላጎት ወይም ባለስልጣን የማላጎበድድ መሆኔን እኔን በሚገባ የሚያውቁ ሰዎች ሁሉ ይረዳሉና የማያውቁኝን ሰዎች ለማሳሳት ባትደሙ መልካም ይመስለኛል፣ አይ ካላችሁ ግን መንገዱን ጨርቅ ያደርግላሁ!! ከማለት በስተቀር ሌላ የምለው አይኖረኝምና ሰላም መንገድ!!